ክብርት ወ/ሮ ወርቅሰሙ ማሞ!

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ዋና አፈ-ጉባኤ!

የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!

ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!

ክቡራትና ክቡራን!

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀፅ 116(2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 እና አንቀፅ 10(2) ለመ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልፅ ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ ይህን ሪፖርት አቀርባለሁ፡፡
2. በዚህ ሪፖርት የመ/ቤታችን የ2009 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ መ/ቤታችን ያከናወነው የ2008 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ እና የ319 መ/ቤቶች የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት እና የክትትል ኦዲት ሪፖርት በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

የ2010 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም፤

የኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ አፈፃፀም

3. በ5ቱ የአቅም ግንባታ ስትራቴጅዎች ማለትም በአመለካከት፤በክህሎት፤በአሰራር፤ በአደረጃጀትና በግብዓት የማብቃትና የልማት አቅሞችን ወደ ተቀራረበ የመፈፀም አቅም የማብቃት ጉዳይ ነው። ከኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ አንፃር በ2010 በጀት ዓመት የአቅም ግንባታ ስትራቴጅዎችን አፈፃፀም 75% በማድረስ፤ የግምባር ቀደም ሰራተኞችን ቁጥር እስከ 50% በማድረስ፤ስራን በተደራጀ መንገድና በለውጥ ፕሮግራሞች አግባብ በመፈፀም የተሻለ የኦዲት ልማት ሰራዊት ለመገንባት ዕቅድ ተይዞ ነበር። ከዚህ አንፃር የመ/ቤታችን ፈፃሚዎች በ4 የልማት ቡድኖችና በ72 የ1ለ5 አደረጃጀቶች ተደራጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል። አደረጃጀቶች በየቀኑ የመረጃ ልውውጥ እና ሳምንታዊ የስራ ላይ ግምገማ በማድረግ፤በየ2 ሳምንቱ በተመረጠ ርዕሰ-ጉዳይ የመማማርና ወደ ተቀራረበ ብቃት ለማምጣትና የመረጃ ፍሰት መፍጠር በቃለ-ጉባዔ የተደገፈ ውይይት በማካሄድ፤ በየደረጃው ግብረ-መልስ እየተሰጠ ለመምራት ጥረት ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም በፈጻሚች መካከል የተቀራረበና የተለወጠ አመለካከት ለማምጣት የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር የጋራ ውይይቶች ተካሂደዋል። በዚህ ደረጃም በልማት ቡድንና በመ/ቤት ደረጃ የተካሄዱ መድረኮች፤ የተደረጉ የስራ ውጤት ግምገማዎችና ውይይቶች ግልጽነትና የአመለካከት መቀራረብ እንድንፈጥርና የተገኙ ግብዓቶችና ክህሎቶችም ለእቅዶቻችን ማሳካት አግዘውናል።
4. ከመልካም አስተዳደር ስራዎች አንፃር በ2010 በጀት ዓመት ዕቅዳችን አስቀድመው የተለዩ ተግባራትን ለማከናዎን ማለትም የሪፎርም ስራዎችን አፈፃፀም አጠናክሮ ከማስቀጠል አጠቃላይ ዕይታ በመነሳት

የህዝብ ከፍተኛ ጥቅም ያለባቸውን የከተሞች መሠረተ ልማት ፈንድ ፕሮግራም (ULGDP) ተጠቃሚ ከተሞች ሂሳብ ኦዲትንና የድህነት ተኮር ሴክተሮችን የዘላቂ ልማት ፕሮግራም (SDG) በጀትን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመከታተል፤ ከህዝብና ከወኪሎቻቸው የሚቀርቡ የልዩ ኦዲት ስራ ጥያቄዎችና ለፍትሃዊ ውሳኔ እንዲግኝ በፍርድ ቤት የሚታዘዙ የኦዲት ስራዎችን ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችለን ለልዩ ኦዲት ስራ አመራር መከታተያ መመሪያ በማሻሻልና የልዩ ኦዲት ስራውን በልዩ ትኩረት በመፈጸም፤ በስራ ላይ ለሚነሱ የኦዲት ስራዎች ቅሬታ የአፈታት አቅጣጫ በማስቀመጥ፤ ቅሬታዎችን ፈጥኖ ምላሽ መስጠት የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት የተሰሩ ጅምር ስራዎች በአበረታችነት የታዩ ናቸው፡፡

5. የውስጥና የውጭ ደንበኞች አገልግሎት አሰጣጣችን በየ6 ወሩ መረጃ በመሰብሰብ ከደንበኞች በአማካኝ 83% እርካታ እንዳለ በዳሰሳ ጥናት የተለየ ሲሆን ይህም በዓመቱ በዕቅድ ከተያዘው አኳያ ሲታይ የዕቅድ አፈፃፀሙ 93% ነው፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ መጠይቅ በማዘጋጀትና በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት ኦዲት አስደራጊዎች በጽሁፍ በሚሰጧቸው አስተያየቶች መሰረት በጥንካሬ የተገለጹትንና የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በመለየት እየተገመገመ እንዲሞላ ከመደረጉም በላይ ለሚዛናዊ ውሳኔና ለግልጽነትና ተጠያቂነት መጠናከር እያገዘ መሆኑን፣ የኦዲት ስራው በየ6 ወሩ ተከፋፍሎ (በኢንትሪም ኦዲት ስልት) መሰራቱ ስህተቶችን በወቅቱ ለማስተካከል ስለሚረዳ በዚሁ እንዲቀጥል የሚሉ ገንቢ አስተያየቶች ናቸው፡፡ በውስንነት ደንበኞች የሰጧቸው አስተያየቶች ሲታዩ በየአመቱ የኦዲት አገልግሎት የማያገኙ ተቋማት መኖርና በህብረተሰቡ ዘንድ የተፈጠረው የሙያው ግንዛቤ ገና ውስንነት ያለበት መሆኑ የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

6. የውጤት ተኮር ሥርዓት(BSC) ከሪፎርም ፕሮግራሞች መካከል ትኩረት ተሰጥቶት በመተግበር ላይ ከመሆኑም ባሻገር አጠቃላይ ውጤቱም ከሌሎች የሪፎርም ስራዎች ጋር ተዳምሮ የመፈጸም አቅሙ የተሻለና መልካም አስተዳደርን ያሰፈነ ተቋማዊ ሁኔታን ማረጋገጥ የሚጠይቅ ነው፡፡ በተለይም ኦዲት በአጠቃላይ የመንግስት አሰራር ግልፀኝነትን የተላበሰና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን የሚያበረክተው አስተዋፅኦ የጎላ በመሆኑ በዚሁ አግባብ መታየት ይኖርበታል፡፡

   በ2010 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ውጤት ተኮር ምዘና መሰረትም መመዘን ከሚገባቸው 304 (ሴት 78) ሰራተኞች መካከል 277 (ሴት 69) ሰራተኞች በምዘናው ያለፉ ሲሆን በምዘናው ካለፉ ሰራተኞች መካከል 92 (ሴት 15) ሰራተኞች ከፍተኛ (33.21%) ያገኙ ሲሆን ቀሪዎቹ 184 (ሴት 54) ሰራተኞች መካከለኛ (66.43%) ደረጃ አግኝተዋል፡፡ አንድ ወንድ (0.36%) ሰራተኛ ዝቅተኛ ደረጃ የተፈረጀ ነው፡፡ ከውጤት ተኮር ስርዓት ጋር በተያያዘ ያሉብን ውስንነቶች ውጤቱን ተከትሎ ወቅታዊ ግብረ-መልስ የመስጠት እጥረት የሚታይ በመሆኑ ከዚህ በመነሳት ለ2ኛው ግማሽ ዓመት ውጤት ተኮር ስርዓት ከችግሮች በሚያወጣ መንገድ ውል ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡

7. የኦዲት ኮሚዩኒኬሽን ስራዎች አፈፃፀም፤

የኦዲት ኮሚዩኒኬሽን ስራችን በዋናነት የፋይናንስ ግልፀኝነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረቱን አድርጎ በሐገራዊ፣ ክልላዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ለመ/ቤቱ ማህበረሰብ ግንዛቤ መፍጠርና የተቀራረበ የአመለካከት አንድነት መፍጠርን ታሳቢ አድርጎ የሚሰራ ስራ ነው፡፡ ከዚህ አንጻርም የክልላችን ሚዲያ ለመጠቀም የሚያስችል ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግና የሙያና የመ/ቤቱ ተልዕኮ የተመለከተ የህትመት ስራዎችን ማሳተምና ተደራሽ ማድረግ የዕቅዳችን አካል የነበሩ ስለአገራዊ፣ ክልላዊና ስለወቅታዊ ኩነቶች ትኩረት ሰጥቶ ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከኦዲት ኮሚዩኒኬሽን የትኩረት ነጥብ አንፃር የመድረክ ዝግጅት በተመለከተ በዚህ 11 ወር ውስጥ በአጠቃላይ 24 ልዩ ልዩ መድረኮች የተካሔዱ ሲሆን ለአብነት የመ/ቤቱ የ2009 ዓ.ም ዕቅድ ክንውን ግምገማና የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ ትውውቅ፣ የሰንደቅ ዓላማ ቀን ክብረ-በዓል፣ የኤች.አይቪ/ኤድስ በዓል ቀን፣ የአጎራባች ክልሎች ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የጋራ ልምድ ልውውጥ፣ የ12ኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን፣ በክልሉ እስከ ወረዳ ለተዋቀረው የኦዲት ግኝት አስመላሽ ግብረ ሃይል ኮሚቴ የጋራ መድረክ፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ የመሠረተ ድንጋይ የተጣለበት 7ኛ ዓመት አስመልክቶና የሠራተኞች ሂስ-ግለ ሂስ መድረኮች ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የኦዲት ሥራ ዕቅድ አፈፃፀም፤

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት አፈፃፀም፤

8. በ2010 በጀት ዓመት በፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ለማከናወን ከታቀደው 309 መ/ቤቶች አንጻር በ11 ወሩ 262 መ/ቤቶችን በማከናወናችን የኦዲት ሽፋን አፈጻጸሙ ሲታይ የዕቅዳችንን 84.7% መፈጸም ተችሏል፡፡

ሽፋን ከበጀት አንፃር እስከ 75% የወጪ በጀት እና እስከ 40% የገቢ በጀት ሽፋን ለማድረስ ታቅዶ ለክልሉ የ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደውን አጠቃላይ በጀት ብር 36.36 ቢሊዮን መነሻ በመያዝ በኦዲት የተሸፈኑ መ/ቤቶች አጠቃላይ በጀት ብር 26.81 ቢሊዮን የኦዲት ሽፋን ያገኘ በመሆኑ አፈፃፀሙ 73.73% ላይ ይገኛል፡፡ የገቢ ኦዲት ሽፋንን በሚመለከት ክልሉ በራሱ አቅም ለመሰብሰብ ከያዘው ዓመታዊ የገቢ መጠን ብር 13.15 ቢሊዮን ላይ ኦዲት የተደረጉ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች ሽፋን የተሰጠው ለብር 1.35 ቢሊዮን በመሆኑ ሽፋኑ 11% ነው፡፡ይህ አፈፃፀም ዝቅተኛ ሲሆን በተለይም በምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤታችንና በዋናው መ/ቤቶችም አንዳንድ ከተሞች የገቢ ሂሳብ ኦዲት ሙሉ በሙሉ ባለመሰራቱ ያጋጠመ ችግር ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ በክልሉ በወቅቱ በነበረው የቁርጥ ግብር ጥናት የዘመቻ ስራ ምክንያት ለኦዲት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠርና የተሟላ ማስረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ ስራው በወጪ ሂሳብ ኦዲት ላይ በማተኮሩ ነው፡፡

በ2010 በጀት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ አሠራሩ ተስተካክሎ በመቀጠሉ ሽፋኑ ከፍ የሚል ይሆናል፡፡

የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት በተመለከተ፤

9. መ/ቤታችን በየዓመቱ ተዘግቶ የሚቀርብለትን የክልሉን የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት እያደረገ አስተያየት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት የ2008 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት ተጠናቆ ‹‹ከዚህ በስተቀር›› የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በግኝቶቹ ላይም የማስተካከያ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ት/ቢሮ በግብረ መልሱ አሳውቋል፡፡ዋና ዋና ግኝቶችም በዚህ ሪፖርት ቀርበዋል፡፡ በሌላ በኩል የ2009 በጀት ዓመት የተጠቃለለው ፈንድ ሂሳብ ተዘግቶ ስለደረሰን የኦዲት ስራው በቢሮ ደረጃ እየተከናወነ ሲሆን ቀሪው የመስክ ስራ በሚቀጥል ይሆናል፡፡

የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት አፈፃፀም፤

10. ከክዋኔ ኦዲት አንፃር በ2009 በጀት ዓመት ዳይሬክቶሬቱን ራሱን አስችሎ በማደራጀትና ወደ ስራ በማስገባት ቀደም ሲል የተጀመሩ ስራዎችን እስከ ታህሳስ 30/2010 ዓ.ም ድረስ የተጠናቀቁ የ6 መደበኛ የክዋኔ ኦዲት ስራዎችን ሪፖርት ወጪ ተደርጎ ለክልሉ ም/ቤት ጉባኤ ለማቅረብ ተችሏል፡፡በተጨማሪም ከታህሳስ/2010 ወዲህ የተጀመሩ 5 የክዋኔ ክትትል ኦዲት ስራዎች ተጠናቀው ሪፖርታቸው ወጪ ተደርጎል፡፡ሌሎች የታቀዱ 10 የመደበኛ ክዋኔ ኦዲት ስራዎች በመስክ ላይ እየተከናወኑ ሲሆን በአጠቃላይ በ11 ወሩ የ14.53 መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማከናወን ታቅዶ በአንፃራዊ ስሌት የ14.22 መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት በመፈጸም የእቅዱን 97.8% ለማከናወን ተችሏል፡፡

የኦዲት ስልጠና፤ክትትልና የሙያ ብቃት ፈቃድ አሰጣጥ አፈፃፀም፤

11. መ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 (2) (ሀ) መሰረት የመንግስት መ/ቤቶችንና የልማት ድርጅቶችን በራሱ ወይም በውክልና ኦዲት እንደሚያስደርግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሂሳባቸውን በግል ኦዲተሮች ኦዲት ላስደረጉትና በማስደረግ ላይ ለሚገኙ የክልሉ መንግስት የልማት ተቋማት፣ የየከተሞች የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤቶችና በማዘጋጃ ቤት ደረጃ ለሚገኙ ከተሞች በቁጥር 13 በሚሆኑት ላይ የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ለግል ሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ፈቃድ መስጠትና የስራ ክትትል ተግባርን በተመለከተ በ11 ወሩ በድምሩ ለ60 (4 ሴት) የሒሳብ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠ ሲሆን የኦዲተር ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ደግሞ ለ15 (2 ሴት) ባለሙያዎች በመመሪያው መሰረት ወደ ግል ስራ እንዲሰማሩ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ወስደዋል፡፡

ስልጠናን በሚመለከት የመ/ቤታችን ኦዲተሮች በቅድመ ስራና በስራ ላይ ሠልጣኝነት ደረጃ ተለይተው ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስራ ተካሂዷል፡፡ ከዚህም መካከል፤ ለጀማሪ ኦዲተሮች በመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት፣ ስለኦዲት ሙያና የሙያው ስነ-ምግባር እና

በመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በስራ ላይ ላሉ የክዋኔ፣የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ማናጀሮችና ፈጻሚ ኦዲተሮች በአዲሱ የገቢ ግብር አዋጅና ደንብ፣ አለምአቀፍ የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ እና በሃብት ዋጋ ግመታ ሙያ ላይ የግንዛቤና ሙያዊ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

እነዚህ ሁሉ የአቅም ግንባታ ስራዎች ባለሙያዎች አለም ዓቀፍ የኦዲት አሠራርና የስነ-ምግባር ደረጃዎችን ጠብቀው ኦዲቱን እንዲሰሩና ውጤታማነታቸው እንዲያድግ ብሎም ክህሎታቸውን ለአዳዲስ ባለሙያዎች በማስተላልፍ የሙያ አገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ ያደርጋል፡፡

የሰው ሃይል መዋቅርና የስምሪት መረጃ፤

12. መ/ቤቱ የደሴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሠራተኞችን ጨምሮ 339 የሰው ኃይል የሚይዝ ድርጅታዊ መዋቅር ያለው ሲሆን አሁን ላይ በሰው ሃይል የተሞላው መደብ 308 ነው፡፡ ይህም የመዋቅሩን 90.85% ይሸፍናል፡፡ ከዚህ ውስጥ 222 (72.54%) አላማ ፈፃሚ እና 86 (27.45%) አስተዳደር ሠራተኞች ናቸው፡፡ በመ/ቤቱ በስራ ላይ ካሉት 308 ሠራተኞች መካከል 227 (73.7%) ወንዶች፣ 81 (26.3%) ሴቶች ናቸው፡፡ ከዓላማ ፈፃሚዎች መካከል 3 ወንድ ተሿሚዎች ናቸው፡፡ ከኃላፊነት አንፃር የሴቶች ተሳትፎ ሲታይ 3 በዳሬክቶሬት ደረጃ፣ 3 በቡደን መሪ (ማናጀር) ደረጃና 1 በኬዝ ቲም አስተባባሪ በአጠቃላይ 7 ሴቶች በመካከለኛ የሃላፊነት ደረጃ የተመደቡ ናቸው፡፡

ከረጅም ጊዜ ሥልጠና አኳያ በ2ኛ ዲግሪ በትምህረት ላይ የሚገኙ ወንድ 29 ሴት 15 በድምሩ 44 ሲሆኑ ከዚህ በተጨማሪ በመጀመሪያ ዲግሪ ወንድ 2 ሴት 2 በአጠቃለይ 4 ሰራተኞች እንዲሁም ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 4 የሚማሩ ወንድ 1 እና 2 ሴት ሠራተኞች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በትምህርት ላይ ካሉት መካከል 19ኙ ሴቶች ናቸው፡፡

የበጀት አፈፃፀምና አጠቃቀም፤

13. በ2010 በጀት ዓመት ለደመወዝ ብር 22,784,450.00፣ ለስራ ማስኬጃ ብር 20,355,799.00 እና ለካፒታል በጀት ብር 1,774,163.00 በድምሩ ብር 44,914,412.00 የተስተካከለ በጀት በመያዝ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡የ11 ወሩ በጀት አጠቃቀም ሲታይ ከመደበኛ በጀት ለደመወዝ ብር 17,844,848.00፤ለስራ ማስኬጃ ብር 18,244,630.00 በድምሩ ብር 36,089,550..72 (ከዓመቱ በጀት 83.66%) ነው፡፡ የካፒታል በጀት ደግሞ የቅድሚያ ክፍያን አካቶ አፈጻጸሙ 868,373.00 (40.10%) ነው፡፡አጠቃቀሙ ዝቅ ያለው በሰኔ ወር መጨረሻ ላይ ለሁሉም ኦዲተሮች ሙያዊ ስልጠና ለመስጠት የተያዘው እቅድ ገና ስለሚፈጸምበት ነው፡፡የካፒታል በጀቱ አጠቃቀም ሲታይ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ለማጠናቀቅና ውል ይዞ ወደ ጥገና ስራው ለመግባት የወሰደው ጊዜ ሰፊ በመሆኑ አፈጻጸሙ

ውስንነት ይታይበታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያዘ ከፍተኛውን ድርሻ (ከ1.3 ሚሊዮን በላይ) የያዘው የአየር ማቀዝቀዣ (ኤር ኮንዲሽነር) መግጠም ሲሆን ይህን ማሽን ከማቅረብ ጋር በተያያዘ በሂደት ላይ ስለሆነ በቀጣይ ማሽኑ ሲገጠም ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ከመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም (PBS-III) ከተመደበልን በጀት 41.7% እና ከከተሞች መሠረተ ልማት ድጋፍ ፕሮግራም (ULGDP-II) ከተመደበልን በጀት ላይም 99% ስራ ላይ ውሏል፡፡

በዚህ የበጀት አፈጻጸም ወቅት የተመደበውን በጀት በፋይናንስ አሰራር እና በተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መሠረት ለመምራት ጥረት የተደረገ ሲሆን በውስጥ ኦዲተሮቻችን አማካኝነት እየተመረመረና ለሪፖርቱ ግብረ-መልስ እየተሰጠ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ጭምር የተላከ ሲሆን የተስተዋሉ የክፍያ፣ የምዝገባና ተያያዥ ግኝቶች ላይ ከስር ከስሩ የማሻሻያ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ የግዥ አፈጻጸሙን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በተያዘው የግዥ እቅድ መሠረት አብዛኛውን ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ ለማከናወን ተችሏል፡፡ የመ/ቤቱ የንብረት አያያዝ በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል እየተደረገ ሲሆን ለኦዲት ምቹ፣ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ሆኖ እንዲተገበር እየተደረገ ይገኛል፡፡

የሴክተር ዘለል ተግባራት አፈፃፀም፤

የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል ስራዎች፤

14. የመ/ቤቱ ሠራተኞች ከየወሩ ደመወዛቸው እያዋጡ በሚያጠራቅሙት የጸረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያ ፈንድ ማህበር ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ባልደረቦችና ማህበሩ ለሚያሳድጋቸው 2 ህጻናት ወርሃዊ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያ ተግባራትን አካቶ መስራት (ሜይንስትሪሚንግ) ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የተላከ ሲሆን በቢሮ ውስጥ ሠራተኞች በየወሩ አንድ ጊዜ ስለቅድመ ጥንቃቄ፣ ስለቫይረሱ ባህሪ፣ የመተላለፊያና መከላከያ ዘዴዎቹ ወዘተ ውይይት እየተደረገና ስለአፈጻጸሙም በየሩብ ዓመት ሪፖርት እየተዘጋጀ ለሚመለከተው በመተላለፍ ላይ ይገኛል፡፡

ስርዓተ ፆታን አካቶ የመስራት እንቅስቃሴ፤

15. ስለስርዓተ ጾታ ተገቢውን ግንዛቤ በመያዝ በሁሉም ስራ አካቶ በመስራትና ሪፖርቶችም በጾታ ተተንትነው የሚቀርቡበት ስርዓት ተዘርግቶ እየተፈጸመ ሲሆን በሴቶች ልዩ ማበረታቻ መመሪያ መሰረት በ11 ወሩ ከተፈፀመው 26 የቅጥር ስምሪት ላይ 8 ሴቶች በልዩ ማበረታቻው መሰረት የተቀጠሩ ናቸው፡፡

ክብርት አፈ-ጉባዔ!

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

ቀጥሎ የ2008 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ (የትሬዠሪ) ሂሣብ ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶችን አቀርባለሁ፤

በክልሉ በተሰብሳቢ የተያዘ ሂሳብ፤

16. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሪፖርት የተመለከተው የክልሉ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 8,856,822,884.28 በወቅቱ ሳይሰበሰብ /ሳይወራረድ/ ተገኝቷል፡፡ከዚህ ተሰብሳቢ ላይም 88.65% የሚሆነው በባለበጀት መ/ቤት ውስጥ ሌሎች (ከአንዱ ለሌላው የተሰጠ)፤ ለስራ ተቋራጮችና ለእቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ፤ ለህብረት ስራ ማህበራት እና ለሌሎች በሚል የተያዘ ተሰብሳቢ ነው፡፡

ስለሆነም ሂሳቡ በእድሜ ተተንትኖ ያልተያዘ በመሆኑ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ማረጋገጥና በ2007 በጀት ዓመት ከነበረው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ምን ያህሉ እንደተወራረደና በበጀት ዓመቱ የተጨመረውና ጊዜው ያላለፈበትን ለይቶ አስተያየት ለመስጠት የማያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የ2008 በጀት ዓመት የተሰብሳቢ ሂሳብ በ2007 በጀት ዓመት ከነበረው የተሰብሳቢ ሂሳብ ጋር በጥቅል ሲነፃፀር በ24.95% ጭማሬ አሳይቷል፡፡

ከዚህ አንጻር በሁሉም ተቋማት (ከክልል እስከ ዞኖችና ወረዳዎች) ያለው የተሰብሳቢ ሂሳብ በየደረጃው በዕድሜ ተተንትኖ እንዲያዝና ለክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ሪፖርት እንዲቀርብ ከማድረግም በላይ በያለበት መወራረድ የሚችለውን ሂሳብ ማወራረድ እንዳለበትና ምክንያቱ ተጣርቶ ሊሰበሰብ፣ ሊወራረድ የማይችለውን ደግሞ ቀደም ሲል በወጣው የተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሰረዝ በወጣው መመሪያ መሰረት ከመዝገብ ሊሰረዝ እንደሚገባ በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

በክልሉ የተያዘ የተከፋይ ሂሳብ፤

17. በክልሉ ውስጥ በአጠቃላይ የሚገኘውን የተከፋይ ሂሳብ ብር 5,022,396,131.27 ሲሆን ይህ የተከፋይ ሂሳብ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየና በ2007 በጀት ዓመት ተይዞ ከነበረው የተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ምን ያህሉ እንደተወራረደ፤ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጨመረውንና የተቀነሰውን በመለየት አስተያየት ለመስጠት አልተቻለም፡፡የ2008 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሳብ ከ2007 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሳብ ጋር በጥቅል ሲነፃፀር በ27% እድገት ያሳያል፡፡

ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ላይ 77.6% የሚታየው ከመንግስት መ/ቤቶች ሌሎች፤ለግንባታ ማስያዥያ እና ለልዩ ልዩ ተከፋዮች በሚል የተያዘ መሆኑን ያሳያል፡፡ ጭማሬው በየበጀት ዓመቱ ካለው የበጀት ጭማሪና የስራ እንቅስቃሴ ስፋት አንፃር እድገት ሊኖረው እንደሚችል ቢጠበቅም ለእድገቱ ምክንያት የሆነው ለረጅም ጊዜ የቆዩ ተከፋይ ሂሳቦች በተለይም በየተቋማቱ ከስር ከስር መከፈል

የሚገባቸው ማለትም የደመወዝና ተያያዥ ተቀናናሾች፤ የጡረታ ተከፋይ፤የንግድ ስራ ትርፍ ግብር ተከፋይ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ የመሳሰሉት ለሚመለከታቸው በወቅቱ ባለማስተላለፉ የተፈጠረ ነው፡፡

ስለሆነም የተከፋይ ሂሳብ በእድሜ ተተንትኖ ሊያዝና በየወቅቱ መከፈል የሚችለውን ሂሳብ ለሚመለከታቸው ሊከፈልና ምክንያቱ ተጣርቶ ሊከፈል የማይችለው /ባለቤት የሌለው/ ሂሳብ ደግሞ ወደ ሀብትነት ተቀይሮ ስራ ላይ ሊውል እንደሚገባ አስገንዝበናል፡፡

የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የመደበኛ በጀት ሂሳብ፤

18. በቢሮው የተጠቃለለው የሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ሁሉም ሂሳቦች መደበኛ ሚዛን ያላቸው ለመሆኑ በናሙና የተመረጡት ሁለት ዞኖች ወርሃዊ ሪፖርታቸው ትክክለኛነት በኦዲት ሲታይ፡-

በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ላይ በድምሩ ብር 11,997,992.39 የተፈጥሮ (መደበኛ) የሂሳብ ሚዛኑን ሳይጠብቅ የተዛባ መልዕክት በሚያስተላልፍ ሁኔታ ሪፖርት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

የተፈጥሮ ሚዛኑን አለመጠበቁ የሂሳብ አያያዝ ስርዓቱን ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ ተዘጋጅቶ የቀረበው አመታዊ ሪፖርት ትክክለኛ መረጃ የማይሰጥና በተጣራ ሃብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ ተገቢው የማስተካከያ ምዝገባ ሊደረግና ለወደፊቱም የሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ወርሃዊ ሪፖርታቸውን ለቢሮው በሚያቀርቡበት ጊዜ ሁሉም ሂሳቦች መደበኛ ሚዛናቸውን መጠበቃቸው እየተረጋገጠ ሊሆን እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በብልጫ ሪፖርት የተደረገ የተጣራ ሀብት ሂሳብ፤

19. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ከ2008 ወደ 2009 በጀት ዓመት ማዞር የሚገባው የተጣራ ሀብት ትክክለኛነት በኦዲት ሲረጋገጥ ቢሮው አስቀድሞ ኦዲት እንዲደረግ የላከው የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሃብትና እዳ መግለጫ "የተጣራ ሃብት" ብር 7,855,162,235.69 የሚያሳይ ሲሆን ነገር ግን በኦዲት ወቅት ሲጣራ ወደ 2009 በጀት ዓመት ሊዞር የሚገባው የተጣራ ሀብት ብር 7,825,395,859.46 ብቻ ስለሆነ ቢሮው በሪፖርት ያስተላለፈው የተጣራ ሀብት መጠን በመብለጥ ብር 29,766,376.22 ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በክልሉ ውስጥ የሌለ ሃብት እንዳለ የሚያሳይ ሆኖ በሪፖርት መተላለፉ ውሳኔ ሰጭውን አካል ስለሚያሳስት የልዩነቱ ምክንያት ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በሪፖርታችን አስገንዝበን ቢሮውም በአስተያየቱ መሠረት በግኝቶች ላይ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ላይ የሚገኝና ጥረቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል በሰጠው ምላሽ አሳውቋል፡፡

ክብርት አፈ-ጉባዔ!

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

መ/ቤታችን ከጥር 1/2009 እስከ ግንቦት 30/2010 ባለው ጊዜ ያከናወነውን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነትና የልዩ ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

20. መ/ቤቱ በዚህ ሪፖርት ያካተተው የ319 መ/ቤቶች የ2009 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ሪፖርት ውጤት ነው፡፡ የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ ማእከል 99 (31%)፣በዞን 13(4%)፤በከተማ አስተዳደሮች 62(19%) ቀሪዎች 145 (46%) በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡

21. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል:: የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎች የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሥሩበትን ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው:: ከኦዲት ስልት አንፃር ከ319 መ/ቤቶች ውስጥ 248 (77.74%) በንሞና እንዲሁም 71(22.26%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማ በመቅረቡ በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸው፡፡

22. **የኦዲት አስተያየት** የ2009 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 319 መ/ቤቶች መካከል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው 236 መ/ቤቶች ናቸው፡፡ ለ14(4%) ***"ንፁህ የኦዲት አስተያየት"***፣ ለ215 (67%)**"ከዚህ በስተቀር"**፣ለ5(2%)**"አጥጋቢ አይደለም"**፣ ለ2(1%) መ/ቤቶች **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ የኦዲት አስተያየቱ ከ2008 በጀት ዓመት የሂሳብ ኦዲት ጋር ሲነፃፀር **"ንፁህ አስተያየት የሚለው"** በ133% መጨመሩ በአንዳንድ መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዙ እና የሀብት አስተዳደር ስርዓቱ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያሳይ ሲሆን ፣**"አስተያየት መስጠት አለመቻል"** በ33% መቀነሱ የኦዲት ማስረጃዎች አቅርቦት ገደብ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያመላክት ነው:: አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ በ51% መጨመሩ ህብረተሰቡ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የመታገል ልምዱ እየጨመረ መምጣቱን እና ስጋተ ኦዲትን መሰረት አድርጎ የመፈፀም ስልት እያደገ መምጣቱን ያሳያል። በሌላ በኩል **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚለው 67% መጨመሩ በአንዳንድ መ/ቤቶች በሀብት አስተዳደር ስርዓቱ ውስጥ ጉልህ ግኝቶች እየተስተዋሉ መሆኑን መረዳት ያስችላል::

የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና የሙያ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻሉ ጉልህና መሰረታዊ ችግር የተገኘባቸው በመሆኑ**"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች፡እነብሴ ሳር ምድርና ጭልጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከላት ናቸው፡፡

መንግስት የመደበላቸውን ሀብት/ገንዘብ/ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመባቸው፤ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው በመሆኑ **"አጥጋቢ አይደለም"**የሚል አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ደ□ሞ ባቲ፣ ሸዋ ሮቢት እና ቆቦ ከተማ አስተዳደሮች፤ ሳይንት እና ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከላት ናቸው፡፡

የኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ አሰጣጥ

23. በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 248 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 63(25.40%) መ/ቤቶች ናቸው፡፡ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር መቀነስ የታየበት በመሆኑ የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲረጋገጥ መ/ቤታችን ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ መስራት እንደለበት አመላካች ሲሆን ምላሽ ያልሰጡ መ/ቤቶችም፤

ክልል/ማዕከል

1 ውሃ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ
2 ሞጣ ማረሚያ ቤት
3 ምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት
4 ገጠር መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ቢሮ
5 አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን
6 መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ መደበኛ SDG 20
7 ጤና ቢሮ SDG 2009
8 ትምህርት ቢሮ SDG 2009
9 ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ
10 አማኑኤል ቴክ/ና ሙያ ማ/ኛከ ኮሌጅ
11 ደ/ማርቆስ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ
12 ደ/ማርቆስ ሪፈራል ሆስፒታል
13 ደባርቅ ሪፈራል ሆስፒታል
14 የቻግኒ ዳልጋ ከብት/ብዜትና ጥበቃ ማዕከል
15 አብክመ ግብርና ምርምር ኢንስቲቲውት
16 ደቡብ ወሎ ዞን ማረሚያ ቤት
17. የደሴ ክልል ጤና ምርምር ላቦራቶሪ ማዕከል
18. ደብረ ብርሃን ግብርና ምርምር ማዕከል

ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር

19. ጃቢ. ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
20. ምዕራብ ጉጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
21. ደንበጫ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
22. ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር

23. ምስራቅ ጎጃም ዞን ፖሊስ መምሪያ
24. ጉንቻ ሲሶ እነብሴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከ6
25. እናርጅ እናውጋ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
26. ደ/ማርቆስ ከተማ አስ/ ገቢዎች ጽ/ቤት
27. ቢቡኝ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
28. ምስራቅ ጉጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
29. ደጀን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር

30. አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
31. ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
32. አዲ አርቃይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
33. ሰሜን ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
34. ምዕራብ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
35. ምስራቅ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
36. ጎንደር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት
37. ገንዳ ዉሃ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/(

ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር

38. ፋርጣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
39. እስቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
40. ለቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ደ/ስ/ማዕከል

አዊ□ ብሔረሰብ አስተዳደር

41. ጃዊ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር

42. ኩታበር ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
43. ከለላ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
44. ተንታ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
45. ቦረና ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
46. ወረባቦ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
47. ደሴ ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል
48. ጃማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል
49. ሀይቅ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር

50. የአርጎባ ልዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
51. አርጡማ ፉርሲ ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
52. ከሚሴ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት

ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር

53. ሰሜን ሸዋ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
54. ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ
55. ሸዋሮቢት ከተማ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
56. ጣርማ በር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል

ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር

57. ዳውንት ወረዳ ን/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
58. ዋድላ ወረዳ ን/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
59. ላሊበላ ከተማ አስ/ን/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
60. ግዳን ወረዳ ን/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
61. ቆቦ ከተማ አስተዳደር ን/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

ዋግኽምራ ብሄረሰብ ዞን

62. ጋዝጊብላ ወ/ን/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል
63. ሰቆጣ ከተማ አገ/ገቢዎች ጽ/ቤት ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

የጥሬ ገንዘብ ጉድለትና ብልጫ

24. የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 5,958,861.73 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 5,923,779.50 ከቀትሞ ገ/ያገሮች የተገኘ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ13 መ/ቤት ብር **9,432,511.52** የተቆጠረ ገንዘብ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ እና በ8 መ/ቤት ቆጠራ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 649,973.62 ተስተውሏል፡፡

ከጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ ብር 45,040.71 የተተካ ሲሆን **ብር** 3,209,866.00 በፍታብሔርና በወንጀል ክስ እንዲሁም ማስረጃ በማጣራት ሂደት ያለ መሆኑ የተገለፀልን ሲሆን በቀሪው ጉድለት ብር 2,703,955.00 ላይ ግን ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 13/2010 ዓ.ም ድረስ ግብረ-መልስ ባለመምጣቱ የተወሰደውን እርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፤

25. በ63 (25.40%) መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡ (ዝርዝራቸው በዋናው ዘገባ ሪፖርት ተመልክቷል፡)

የገቢ ሒሳብ ኦዲት ውጤት

የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት የገቢ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣

26. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ2 መ/ቤቶች ብር 46,020.00 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡
   - **በጉባ ላፍቶ ወረዳ ተራማጅ የገበሬዎች ሁለ ገብ ኅ/ሥ/ማኅበር ብር 45,000.00** የተሰበሰበን ገንዘብ በገቢ ደረሰኝ ቅጠል ላይ በመደለዝ ገቢው እንዳይያዝ በማድረግ ለግል ጥቅም የዋለ፣
   - **በደሴ ከተማ አስተዳደር የፒያሳ ክ/ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 1,020.00** ተወካይ ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከታህሰስ 2007 እስከ ታገዱበት ቀን ድረስ ከትራፊክ ደንብ ገቢ ሲሰበስቡ በኦርጅናል የገቢ ደረሰኝ ቅጠል የተሰበሰበውን ገቢ በቀሪ ደረሰኝ ቅጠሉ ላይ ዝቅ አድርጎ በመፃፍ ሂያጅ እና ቀሪ የደረሰኝ ቅጠሎችን

በማበላለጥ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ናቸው፡፡

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት አካላት የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ብናሳስብም የክስ ሂደቱ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አልተገለፀልንም፡፡

27. **ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ፣**

- **የአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 92,942.29** ቢሮው በጠገዴ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ሲያስገነባ እና 2ኛ እና 3ኛ ዙር ክፍያዎች ለስራ ተቋራጮች ሲፈጽም መቅረብ ከሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ በታች ቀርቦ ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ፣
- **እንጅባራ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 59,596.70** በእንጅባራ ከተማ ቀበሌ 01 እና 02 የዲች ቦይ እና የእንጅባራ ሁለ-ገብ እስታዲዮም ግንባታዎች ተከናውነው ለስራ ተቋራጮች ክፍያ ሲፈፀም ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ፣
- **ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 44,797.92** ለህዝብ ግንኙነት እና አደረጃጀት አማካሪ ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል የአዳራሽ ግንባታ እና በተለያዩ ቀበሌዎች ለተገነቡ ት/ቤቶች ለስራ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈፀም ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

ከብር 40,000.00 በላይ ክፍያ ሲፈጽሙ ከአቅራቢ ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልቀረበለት ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተስተዋለባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ ተቋራጮች ታክሱን ለገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ አድርገው ማስረጃ እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት እያስገነዘብን ታክሱን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆኑ በሚመለከተው የፍትህ አካል ክስ በመመስረት ከተጠቃሚው የተሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ገቢ፤

28. የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ 319 መ/ቤቶች ውስጥ በ79 መ/ቤቶች ብር 99,382,640.47 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል። ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 70,044,570.76(70.48%)፣ምስ/ጎጃም ዞን አስተዳደር ብር **12,437,052.77** (12.51%) እና ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር **6,474,109.96** (6.51%) ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ዉስጥ ብር 549,432.98(0.55%) ብቻ ስለመሰብሰቡ በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ብር 98,833,207.49 የተሰበሰበ ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ሰኔ 13/2010 ዓ/ም ድረስ መልስ ያልተሰጠበት ነው፡፡

ያልተሰበሰበ 2% የንግድ ትርፍ ግብር፤

29. በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ እንደተመለከተው ከተወሰነ መጠን በላይ የሆነ የእቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሡብሰብ የሚገባው 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር ከ11 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 285,183.22 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ገቢው ከየሚመለከታቸው ላይ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ባሳሰብነው መሰረት ብር 132,735.40 (46.54%) መሰብሰቡን የሚገልጽ ማስረጃ በግብረ መልስ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 152,447.82 (53.46%) ያልተሰበሰበ የንግድ ስራ ትርፍ ግብር በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም።

ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች

30. ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ65 መ/ቤቶች ብር 42,515,120.57 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከፍተኛውን የሚይዙት፡-

የጎንደር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 10,068,690.24 ብዛት 320.86 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ከሚሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,333,503.28 የያዙ የውስጥ ገቢ መሰብሰቢ ደረሰኞች፣ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,202,420.30 የያዙ የመደበኛ፣የእንስሳት ጤና እና የስፖርት ምክርቤት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ጓንጓ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,216,641.68 የስፖርት ምክር ቤት፣የመደበኛ እና የመሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ባሶ ሊበን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,190,410.49 ብዛት 94-ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት፣5-ጥራዝ የመናኸሪያ ሂሳብ፣7-ጥራዝ የእንስሳት ጤና ሂሳብ፣ብዛት 402-ጥራዝ የመሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,101,861.00 የመሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር እና የስፖርት ምክር ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣አብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ብር 1,675,009.96 የመናኸሪያ አገልግሎት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣

በጃዊ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,668,034.86 የያዙ ብዛት 4-ጥራዝ የመደበኛ እና 147.38 ጥራዝ የመሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣እስቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,578,650.00 የእርሻ ስራ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ወልድያ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 1,280,136.33 የያዙ ብዛት 425 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ባቲ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,252,907.05 የያዙ ብዛት 32 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ ኤፍራታና ግድም ወረዳ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,078,745.46 የያዙ የመደበኛና የስፖርት ም/ቤት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ስራ ካልቀረቡት ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙ ናቸው፡፡

ለኦዲት ስራ ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ማጭበርበር ተሰርቶባቸው ይሆናል የሚል ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ባሳሰብነው መሰረት ብር 386,714.73 (0.91%) የያዙ ገቢ ደረሰኞች ብቻ ለውስጥ ኦዲት ቀርበው የተረጋገጡ ስለመሆናቸው በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ለቀሪው የተወሰደው እርምጃ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር (ሰኔ 13/2010 ዓ/ም) ድረስ ምላሹ አልተገለፀም፡፡

የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት

በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ

31. የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ108 መ/ቤቶች ብር 1,651,173,172.00 በወቅቱ የፋይናንስ አሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ/ ከመዝገብ ሳይሰረዝ ተገኝቷል፡፡ ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ/የመወገጃ ጊዜ እንዳላቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በቢሮው በቁጥር 6/2004 በክፍል 4 በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አንዳንድ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ባሳሰብነው መሰረት ስለተወሰደው እርምጃ በተሰጠው ምላሽ ብር 16,408,138.42(1%) ከኦዲት በኋላ የተሰበሰበ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በቀሪው **ላይ** ስለተወሰደው እርምጃ ባለመገለጹ ይህ ዘገባ እስከተሰራበት ሰኔ 13/2010 ዓ.ም ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ አልታወቀም፡፡

    በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በኦዲት ወቅት በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ከ3ኛ ወገን (ይሰበሰብባቸዋል ተብሎ ከተያዙ አካላት) ለማረጋገጥ ከተጠየቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች መካከል በ13 መ/ቤቶች ብር 74,551,286.67 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡

32. ከላይ ከተመለከተው ተሰብሳቢ መካከል በ4 መ/ቤቶች ብር 39,833,489.74 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣ መቼ እንደተሰጠ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ የሚሳይ ማስረጃ ሳይኖር በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ይኸው ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ቃሉ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 26,338,075.98፣ ኩታበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ ማዕከል ብር 7,581,923.06፣የቋራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 4,461,859.28፣አርጎባ ልዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ ማዕከል ብር 1,451,631.42 ናቸው፡፡

በመሆኑም ለሂሳቡ ትክክለኛ ዝርዝር ደጋፊ ማስረጃ ካለ ተጣርቶ በየባለዕዳዎቹ ስም ተለይቶ እንዲያያዝና ክትትል ተደርጐ እንዲሰበሰብ ወይም በመመሪያው መሰረት ከመዝገብ እንዲሰረዝ የኦዲት አስተያየት

ተሰጥቷል፡፡ ሆኖም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ሰኔ 13/2010 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚገልጽ ምላሽ አልደረሰም፡፡

33. በተጨማሪም በ46 መ/ቤቶች ብር 497,265,160.61 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ በባለቤቱ ስም ተለይቶ በሚያሳይ መልኩ የተመዘገበ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ/ለማስወገድ የማያስችል በመሆኑ የተሻሻለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየስሙ የተቀፅላ ሌጀር ሊዘጋጅለትና ክትትል እየተደረገ ሊሰበሰብ/ከመዝገብ ሊሰረዝ/ እንደሚገባው በሪፖርታችን ብናሳስብም ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መልስ ብር ብር 2,325,428.68 (0.47%) ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ሂሳብ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት (ሰኔ 13/2010 ዓ.ም) ድረስ የተሰጠ ግብረ መልስ ባለመኖሩ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

የወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፤

የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች

34. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል በ15 መ/ቤቶች ብር 2,419,885.58 የተለያዩ የማጭበርበር ድርጊቶች ተፈፅሞበት ተገኝቷል፡፡ ከብር 40,000.00 በላይ የገንዘብ መጠን የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,310,562.40** በ2007/2008 የምርት ዘመን ለተከሰተው ድርቅ ለአርሶ አደሮች የሚከፋፈል የሽንብራ ዘር ግዥ ሲፈፀም ያልተገዛ የሽምብራ ዘር እንደተገዛ በማስመሰል፣ለአርሶ አደሮች ሳይሰራጭ እና ሳይደርሳቸው እንደወሰዱ ተደርጎ በሰነድ ላይ በማስፈረም ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣
- **የቦረና ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር 424,908.70** ከአስተዳደር ጽ/ቤት በጀት 66 ለሚሆኑ የቀበሌ ፖሊሶችና ስራ አስኪያጆች ስልጠና ሳይሰጥ የስልጠና መከታተያ የስዓት ፊርማ በማዘጋጀት እና ፊርማቸውን አስመስሎ በመፈረም የሀሰተኛ የክፍያ ሰነድ በማዘጋጀት ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 61,320.00፣ከጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በጀት የጤና አጠባበቅ ጣቢያና ጤና ኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ስልጠና ሳይሰጥ የስልጠና መከታተያ የስዓት ፊርማ በማዘጋጀት እና ፊርማቸውን አስመስሎ በመፈረም የሀሰተኛ የክፍያ ሰነድ በማዘጋጀት ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 189,693.00፣ ለመስተንግዶ አገልግሎት ተገዝተዋል በሚል የስጋ በሬዎች ሳይገዙ የንብረት ገቢና ወጭ ደረሰኝ በመቁረጥ የሀሰተኛ የክፍያ ሰነድ በማዘጋጀት ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 41,866.00፣ ከአስተዳደር ጽ/ቤት በጀት አረብ አገር ሲኖሩ ለነበሩ ሶስት ግለሰቦች ከባድ የንብረት አዳጋ ደርሶባቸዋል በሚል ሳይከፈላቸው ሀሰተኛ የክፍያ ማስረጃ በማዘጋጀት ተፈጽሞ ለግል ጥቅም የዋለ ብር

95,000.00፣መስክ ሳይወጣ በመደበኛ ስራ ቢሮ ውስጥ በዋሉበት ሁኔታ የሀሰተኛ የክፍያ ሰነድ በማዘጋጀት አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 37,029.70፣

- **ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር 146,958.84** ለ5 መምህራን የሀምሌ እና ነሐሴ ወር/2008 ዓ.ም ደመወዝ ክፍያ ሳይፈፀም እንደተከፈለ በማስመሰል የክፍያ ሰነዶችን በማዘጋጀት በብልጫ ፀድቆ ለግል ጥቅም የዋለ የደመወዝ ሂሳብ ብር 9,626.84 እና ህጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላቸውን አቅራቢዎች የንግድ ስራ ፈቃዳቸው አግባብነት የለውም በማለት ከግዥ ውድድር ውጭ እንዲሆኑ ተደርጎ አንድ አቅራቢ ብቻ በግዥ ሂደቱ ላይ በብቸኝነት እንዲወዳደር ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር በተጋነነ ዋጋ በልዩነት የተፈፀመ የግንባታ ግብዓት ግዥ ብር 137,332.00፣
- **የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር 133,500.00** የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ የዶዘር ኪራይ አገልግሎት ለማቅረብ ውል ከተወሰደ በኋላ አላግባብ ከውል በላይ የተከፈለ የዶዘር ኪራይ እና ከውል ስምምነት ውጭ አላግባብ የተከፈለ የሎቬድ ማስጫኛ ሂሳብ፣
- **የአምባሰል ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ብር 130,484.28** ለመሰናዶ ትምህርት ቤቱ መማሪያ ሁለት ክፍሎች ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ላልተሰራ የግንባታ ስራ ለተቋራጭ የተከፈለ ሂሳብ፣
- **ቅዱስ ነአኩተ ለአብ 1ኛ ሙሉ ሳይክል ት/ቤት ብር 79,470.50** ለት/ቤቱ ግንባታ አሸዋ ግዥ ሲከናወን ከተገዛው አሸዋ መጠን በላይ(ውጭ) ለማጓጓዣ በሚል የተከፈለ፣ያልተገዙ የተለያዩ የግንባታ ግብዓቶች ግዥ ተከናውኗል በሚል ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ እንዲሁም በጨረታ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን አቅራቢ በመተው በተጋነነ ዋጋ ከሌላ አቅራቢ ድርጅት የተፈፀመ የግንባታ ግብዓት ግዥ እና ለኮንትራት ሰራተኞች ሳይከፈል እንደተከፈለ በማስመሰል የሂሳብ ማስረጃ በማቅረብ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣
- **የመተማ ወረዳ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ብር 78,981.82** ከተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ለሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች እና የመንግስት ሰራተኛ ያልሆኑ ግለሰቦች የመንግስት ሰራተኛ እንደሆኑ በማስመሰል የመስክ ስራ ለሰሩበት በሚል ለተቋሙ ምንም አይነት ስራ ሳይሰሩ አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 44,647.00፣በተመሳሳይ ቀን በድጋሜ አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል እና የተለያዩ የቢሮ እቃዎችን ለማሟላት በሚል በውሎ አበል መልክ ገንዘብ ወጭ በማድረግ እና በማስደረግ እቃው ሳይገዛ ለግል ጥቅም የዋለ ብር 20,439.50፣ላልተገዛ ነዳጅ አላግባብ የተከፈለ እና ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 13,895.32፣

- **ምዕራብ በለሳ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር 46,583.75** በ2008 በጀት ዓመት ከጣላ-ፈረፈር፣ከአርባያ-ሮቢት እና ከሮቢት-ሰላሬ ቀበሌዎችን በመንገድ ለማገናኘት በማሰብ የመንገድ ስራ ሲሰራ ላልተሰራ ስዓት አላግባብ ለዶዘር ኪራይ የተከፈለ ሂሳብ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት ኃላፊዎችና ሰራተኞች የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል

በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 93,099.75 (3.69%) የተመለሰ ሲሆን ብር 1,976,102.76 በፍታብሔርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ ያለ መሆኑን በሪፖርት ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አልታወቀም፡፡

ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

35. በ33 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 5,506,089.40 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ እንዲደረግ ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በታክሱ ሰብሳቢዎቹ እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለግብር አስገቢው መ/ቤት ፈሰስ መደረጉ እንዲረጋገጥ ሆኖ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀረት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

አላግባብ የተፈተመ ክፍያ፤

36. ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ108 (34.17%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 44,222,087.64 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 500,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- **ጤና ጥበቃ ቢሮ የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ሂሳብ ብር 19,826,571.29** በቢሮው ለሚገነቡ ሆስፒታሎች የፈርኒቸር ግዥ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣በጃማ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ግንባታ 6ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተፈፀመ፣
- **ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,909,443.25** የቢሮ ህንፃ ግንባታ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ሲፈጸም በውለታ ስምምነት ላልተካተተ ስራ የተከፈለ፣ በመደበኛ ስራዎች ቢሮ ውስጥ ውለው እያለ ላልተሰራ ስራ የተከፈለ ውሎ አበል እና ለትምህርት ቤት አስተዳደር እና ላብራቶሪ ህንጻ ግንባታ ክፍያ ሲፈጸም አላግባብ በብልጫ የተከፈለ፣
- **ሸበል በረንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,705,446.44** ለጤና ጥበቃ ጽ/ቤት አንድ ባለሙያ በዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ለተከታተሉበት የትምህርት ክፍያ ሲሸፈን ከበጀት ዓመቱ ውጭ ወደኋላ በመሄድ አላግባብ የተሸፈነ ክፍያ፤ ለወባ መከላከያ ኬሚካል ስርጭት ለተሳተፉ ሰራተኞች ላልሰሩበት ስራ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፤ላልተካሄደ ስልጠና አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል፤የምዝን

ጤና አጠባበቅ ጣቢያ እና በዋን ዋሽ ፕሮግራም በጀት የተሰራ የጋራ መፀዳጃ ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ከስራ ዝርዝር ውጭ የተከፈለ ክፍያ፤ በአፋፍ አካባቢ ለተገነባው የህዝብ መፀዳጃ ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ተጨማሪ የስራ ውል ሳይኖር የተፈፀመ፤ የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ ሲፈፀም ከስራ ዝርዝር ውጭ እና የለውጥ ስራ ሲካሄድ ተጨማሪ ስራው በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የተከፈለ ክፍያ፣

- **አዊ ብሔረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 2,827,836.45 ስልጠና ሳይሳተፉ እንደተሳተፉ በማድረግ አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል፤ለስልጠና መሄጃና መምጫ ቀናት አላግባብ የተከፈለ የትራንስፖርት ክፍያ፤ የአስተዳደር ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ 5ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ከውለታ በላይ በብልጫ የተከፈለ፣
- **ሰቆጣ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,960,048.90 በከተማው ውሃ ላልገባባቸው መስመሮች የውሀ መስመር ዝርጋታ ለመፈፀም ውል የተያዘ ሲሆን ምንም ስራው ሳይሰራ የተፈጸመ ክፍያ እና ላልተሰራ ስራ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ቡሬ ተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,139,402.85 አንድ እስካቫተር ከነጃክ ሀመር ግዥ ሲፈፀም በብልጫ የተፈፀመ፤የመሀር ሰብል ስልጠና እና ሌሎች ስልጠናዎች ሲሰጡ ላልሰለጠኑ ግለሰቦች እንደሰለጠኑ ተደርጎ ተጨምሮ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር** 1,101,628.12 ከስልጠና ቀናት በላይ የተከፈለ የስልጠና አበል፤ከአገር ውጭ ለተደረገ የስልክ ጥሪ አላግባብ የተከፈለ ሂሳብ፣ለተለያዩ ሆስፒታሎች የመድሀኒት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ የፀደቀ ወጭ፣በዳዋ ጨፋ ወረዳ የወልዲ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **አብክመ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ብር** 941,773.91 አዲአርቃይ መንገድ ስራ ደጃች ሜዳ መንገድ ስራ ፕሮጀክት 31ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፤
- **አዲአርቃይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 520,616.93 በዛሪማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ መፀዳጃ ቤት እና የሻዎር ቤት ግንባታ ለማከናወን ግልጽ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊ ድርጅት ሲመረጥ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተቋራጭ መምረጥ ሲገባ ከመመሪያ ውጭ ውድቅ በማድረግ ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበን ተቋራጭ በመምረጥ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ፤የተለያዩ ሰራተኞች ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ለመስክ ስራ የሄዱበት በሚል መስክ ሳይወጣ የተከፈለ ውሎ አበል፤ስልጠና ሳይሳተፉ እንደተሳተፉ በማድረግ አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል፤በውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት በዝዋ፣ በሀዋዛ፣ በአራ፣ቀበሌዎች በሚገኙ የተለያዩ ጎጦች የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ እና የምንጭ ማጎልበት ስራ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም መከፈል ከሚገባው በላይ በብልጫ የተከፈለ፣

የ2009 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ከ2008 በጀት ዓመት ብር 43,200,227.99 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ5 ሲቀንስ በገንዘብ መጠን ግን በብር 1,021,859.65 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ

ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 4,863,846.08 (11%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ስለመተካቱ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 13/2010 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡ ይህም በተለያዩ መንገዶች አላግባብ ክፍያዎችን መፈጸም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር መባባሱን ያሳያል፡፡

የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

37. ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በ52(16.30%) በድምሩ ብር 50,268,896.58 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ ከብር 1.5 ሚሊዮን በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- አብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ብር 6,537,164.53 ለጎንደር እና ደሴ ትራፊክ ኮምፕሌክስ አስፓልት የማንጠፍ ስራ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም ለለውጥ ስራው ውል ሳይያዝ የተፈጸመ ክፍያ፣ እንጅባራ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 5,699,771.05 ለከተማው ሁለ-ገብ ስታዲዮም አጥር፣ለዲችቦይ፣ በተለያዩ አካባቢዎች ለተገነቡት ግንባታዎች ከ1ኛ-3ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ዝርዝር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ፤ ሸዋ ሮቢት ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 5,640,407.30 በከተማ ውስጥ በተለያዩ ቀበሌዎች ለተሰራው የኮብል ስቶን ክፍያ ሲፈፀም የግንባታ ስራ ልኬት ወረቅት እና የስራ ዝርዝር ሳይቀር የተፈጸመ፣መካነ ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 5,071,970.35 ቴክኒክና ሙያ ላስገነባው የሸድ፣ በ02 ቀበሌ ለሚገነባው አጥር፣ከአሮጌው ኮብል እስከ ህዳሴ ሆቴል ለሚሰራ ኮብል ስቶን፣ከአራዳ እስከ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ድረስ የካናል እና የድንጋይ ግንብ ስራ፣የእንስሳት ማቆያ ቤት ግንባታ ሲከናወን የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይቀርበ የተከፈለ ክፍያ፣ ደብረ ብርሀን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 4,551,737.72 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ የመጀመሪ ዙር ክፍያ ሲፈፀም እና በቀበሌ 02 ለተሰራ ኮብል ስቶን የግንባታ ስራ ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣ ቋራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,134,101.35 በማህዲድ፣ በቦሊ፣ በሻሆ፣ አሻ ጎጦች የምንጭ ማጎልበት ግንባታ፣የቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ወርክሾፕ ግንባታ፣ የአስተዳደር ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ፣በተለያዮ የገጠር ቀበሌዎች የእጅ ውሃ ጉድጓድ ግንባታ ሲፈፀም የግንባታ ስራ ዝርዝር ሳይቀርብ የተፈፀመ፣ዳንግላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,611,787.21 በተለያዩ ቀበሌዎች የዲች ቦይ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተከፈለ፣ በንጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,789,843.23 የአብስላ-አደጋ የጠጠር መንገድ ግንባታ፣ ለቲሊሊ፣ ለጉሻ እና ለአሽፋ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የእናቶች ማቆያ ክፍል ግንባታ፣የፖሊስ ጽ/ቤት የአጥር ግንባታ፣ግብርና-አዳጋ የድልድይ ስራ፣የቲሊሊ ከተማ የመናኸሪያ በር ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተከፈለ፣ በየዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,526,938.09

የመለብ፣ለገዘይ ሜዳ፣ለታችአምቢ፣ለልዋሬ ማሪያም፣ለመደባይ 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመፀዳጃ ቤት ግንባታ የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም እና አበል ውሀ ወንዝ፣ወንበር ወንዝ፣መብሉክ ወንዝ የመስኖ ካናል ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተከፈለ፤ በመልባ ቃራ ቀበሌ የምንጭ ማጎልበት የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በሚመለከተው አካል ርክክብ ሳይፈፀም የተከፈለ፤

በአጠቃላይ ስራው ስለመከናወኑ የሚያሳዩ የስራ ልኬት ወረቀት /የክፍያ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ ሳይቀርብ እና ርክክብ ሳይፈፀም ክፍያ ተፈፃሞ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንድስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለ ከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 7,788,221.06 (15.49%) የተተካ/የተረጋገጠ ሲሆን ቀሪው ሂሳብ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 13/2010 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ

38. ማንኛውም ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባ ይህን በመተላለአ በ65 (20.38%) መ/ቤቶች የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 25,179,267.38 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት □አ□ ተ□□ሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር 55,161,544.30 ጋር ሲነፃፀር በ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር 2 የጨመረ ሲሆን በገንዘብ መጠን ግን በብር 29,880,484.92 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ ያለው ችግር እየተሻሻለ መምጣቱን ያመለክታል፡፡፡ ስለሆነም ክፍያውን የፈፀሙት መ/ቤቶች በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን የማያመላክት በመሆኑ ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን ብር 2,320,815.61 ከኦዲት በኋላ ማስረጃ የቀረበለት መሆኑን በሪፖርት ግብረ-መልስ የተገለፀ ሲሆን በቀሪው ላይ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 13/2010 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡

ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች፤

39. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ26 (8.15%) መ/ቤቶች ብር 45,622,027.66 የያዙ የወጪ ማስረጃዎች

ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 156,579.80(0.34%) ከኦዲት በኋላ ማስረጃ ቀርቦ በውስጥ ኦዲተር የተረጋገጠ መሆኑ በግብረ መልስ ተገልጿል፡፡ ከፍተኛ ወጪ ይዘው ማስረጃ ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከልም ከብር 300,000.00 በላይ የያዙ መ/ቤቶች፡-

- ባቲ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 10,812,126.85፣ኤፍራታና ግድም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 8,236,804.76፣ደንበጫ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 5,722,094.82፣ምስራቅ በለሣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 4,110,722.00፣መርሳ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,564,350.29፣ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,362,102.43፣ጭልጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,066,954.51፣ አንዳቤት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,452,397.76፣በረኸት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 979,007.04፣ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 919,570.77፣ላይ አርማጭሆ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 571,754.53፣ጎንደር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 415,932.64፣ጁሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 402,846.03 ሲሆኑ፣

ማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ድርጊት አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ይሁንና በቀሪው ላይ ስለተወሰደው እርምጃ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 13/2010 ዓ.ም ድረስ የሚያሳይ ምላሽ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም፡፡

የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሒሳብ

40. የእቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ140 (43.88%) ብር 119,427,957.14 ዥ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ሥርዓት የሚጠይቀውን መሥፈርት ሣያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡የግዥ አፈጻፀም ችግሮች ጎልቶ የሚታይባቸው ከብር 1.2 ሚሊዮን በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- **ጤና ጥበቃ የዘላቂ ልማት ማስፈፀሚያ በጀት ብር 59,227,847.10** በክልሉ ለሚገነቡ ሆስፒታሎች የፈርኒቸር ግዥ እና ለጎንደር ከተማ ዞናል ሆስፒታል ግንባታ የ11ኛ እና የ12ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ፣
- **አብክመ ግብርና ቢሮ ብር 4,483,226.89** ለእንስሳት ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ለአዳራሽ አገልግሎት የሚውል የወንበር ግዥ ሲፈፀም አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በፕሩፎርማ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣የፎቶ እና የቪዲዮ ካሜራ ግዥ ሲፈፀም አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በውስን ጨረታ የተከናወነ

ግዥ፤የነፍስ ወከፍ የጤፍና የማዳበሪያ መዝሪያ መሳሪያ ግዥ ሲፈፀም ንብረቱ ገቢ ስመሆኑ የሚያሳይ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ ተፈጽሞ የተገኘ ግዥ፣

- **አብክመ ስራ አመራር አካዳሚ ብር** 3,121,196.05 የደንብ ልብስ፣የመስተንግዶ፣የመኪና መለዋወጫ፣ የቲሸርት ህትመት፣የመኪና ሽድ ላሜራ ግዥ ሲፈፀም አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ፤ የወንበር ጥገና ግዥ ሲከናወን በግዥ መመሪያው መሰረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ድርጅት መፈፀም ሲገባው ተመዝጋቢ ካልሆነ አቅራቢ የተፈፀመ ግዥ፤የኤር ኮንዲሽነር፣የባነር ግዥ ሲፈፀም ህጋዊ ንግድ ስራ ፈቃድ ካላቀረበ አቅራቢ የተፈፀመ ግዥ፣
- **አብክመ ርዕሰ-መስተዳድር ጽ/ቤት ብር** 2,178,006.12 የተለያዩ የህንፃ መሳሪያዎች፣አይሲቲ እቃዎች፣የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ተገዝተው ገቢ ሲሆኑ በስፔሲፊኬሽናቸው መሰረት ገቢ መደረጋቸው በባለሙያ ያልተረጋገጠ፤ ለሁለተኛው የዲያስፖራ ቀን በአል አከባበር ስካርፕ፣የአልጋ እና የመስተንግዶ ግዥ ሲፈፀም የተጠቃሚዎች የስም ዝርዝር ሳይቀርብ፣ያለግዥ መጠየቂያ እና አሳማኝ ምክንያት ሳይቀርብ በውስን ጨረታ መገዛት ሲኖርበት በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ፤የባህር ዳር ከተማ መገለጫ የያዙ የቁልፍ መያዣዎች ግዥ ሲፈፀም ህጋዊ ንግድ ስራ ፈቃድ ከሌለው አቅራቢ ተፈጽሞ የተገኘ፣
- **የላሊበላ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር** 1,830,549.05 የተለያዩ የውሀ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፀም ከመመሪያ ውጭ ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ ግዥ፣
- **ሚዳና ወረሞ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,488,817.24 የጽዋት ዘር፣የአፈር ማመላለሻ ተሽከርካሪ አገልግሎት እና የጽ/መሳሪያ ግዥ ሲከናወን አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ፣
- **በረኸት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,462,523.34 ለውሀ ጽ/ቤት የውሀ እቃዎች ግዥ ሲፈጸም ያለግልጽ ጨረታ በቀጥታ የተገዛ፣የግዥ መጠየቂያ ያልቀረበለት የእንጨት ግዥ፣የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች የቋሚ እቃዎች ሲገዙ ከግዥ በፊት የንበረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት፣
- **መካነ ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,414,520.07 ለሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውል ኤሌክትሮኒክስ፣ልዩ ልዩ መሳሪዎች እና የጽ/መሳሪያዎች ከአቅራቢ ድርጅቱ ጋር የውል ስምምነት ሳይያዝ የተፈጸመ እና የእቃ ጥራቱ በባለሙያ ሳይረጋገጥ የተከፈለ፣
- **ምዕራብ በለሳ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር** 1,386,744.32 የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት፣አስተዳደርና ፀጥታ ጽ/ቤት፣ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት፣ግብርና ጽ/ቤት እና ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ተሽከርካሪዎች የጥገና የእጅ ዋጋ ፣መለዋወጫ ዕቃዎች እና ጎማ ግዥ ሲገናወን አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በፕሮፎርማ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ እና የብልሽቱ አይነት እና መጠን እንዲሁም ተጠግኖ ሲወጣ ስለመጠገኑ በባለሙያ ሳይረጋገጥ የተከፈለ ሂሳብ፣
- **ፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል ብር** 1,379,434.06 የግዥ ህጉን በመጣስ በቀጥታ ውል ተይዞ ለተከናወነ ግንባታ የተከፈለ የተጨማሪ ስራ እና ያለለውጥ ስራ ትዕዛዝ ከተያዘው ውል በላይ ተጨምሮ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ፣

- **ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ስ/ማዕከል ብር 1,367,743.54** ለሴክተር መ/ቤቶች የመኪና መለዋወጫ እቃዎች ግዥ ሲፈፀም፣ ከወረዳው በርበርና ገልገሎ ቀበሌ ጀውሀ ወንዝ የጎርፍ መከላከያ ሲሰራ ያለጨረታ የተከናወነ አገልግሎት ግዥ፣
- **ጎንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,327,250.99** የህትመት ግዥ፣የመስተንግዶ፣የተሽከርካሪ መለዋወጫ እቃ፣የድሬኔጅ ግንባታ ሲከናወን ያለአሳማኝ ምክንያት በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ፤
- **ሳይንት ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 1,239,503.75** የአስተዳደር ጽ/ቤት የተሽከርካሪ ጥገና፣የጽ/መሳሪያ ግዥ ሲከናወን አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ ግዥ፣የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች የጽ/መሳሪያ እና የግንባታ እቃዎች ግዥ ተፈጽሞ ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት፣ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የግዥ ህጉን በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች አሣስበናል፡፡

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 85,767,773.50 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ11 እና በገንዘብ መጠን በብር 33,660,183.64 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል በኩል ችግሮች እንዳሉባቸው ያመላክታል፡፡

የተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ፤

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣

41. የ2009 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ38 መ/ቤቶች ብር 112,483,522.92 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቼ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መልስ እንደተረጋገጠው ብር 4,022,696.53 (3.58%) የተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት መሆኑ በግብረ መልስ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 108,460,826.39 ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 13/2010 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ ባለመኖሩ ለምን ያህሉ ገንዘብ ተቀጽላ ሌጀር እንደተዘጋጀ ማወቅ አልተቻለም፡፡

የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት

42. የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፣ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሒሳቡም በመ/ቤታችን ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 248 መ/ቤቶች መካከል በ110(44.35%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር ግድፈቶች በማረም ሊከሰት የሚችለውን ከፍተኛ የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይከሰት ተገቢው የንብረት አስተዳደር፣አያያዝና አጠቃቀም በየመ/ቤቱ እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

የንብረት ሂሳብ ጉድለት

43. የ2009 በጀት ዓመት ሒሣባቸው ኦዲት ከተደረገ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 13,649,559.32 ጉድለትና ማጭበርበር የተገኘ ሲሆን ጉድለት/ማጭበርበር የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር፡-

- **አማራ ህንፃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት** ብር 12,449,092.81 የንብረት ክፍል ሰራተኛ የነበሩት ከ1/8/2000-4/11/2005 ድረስ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ ዋጋው የታወቀ ጉድለት እና ዋጋው ያልታወቀ የንብረት ጉድለት መጠን 25,840.66፣
- በልዩ ትዕዛዝ የተሰራው **የጥቁር አባይ ትራንስፖርት ድርጅት** ብር 692,634.81 የድርጅቱ የነዳጅ ማደያ ኃላፊ የሆኑት ከ05/01/2005-29/6/2007 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- የድሀና ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ብር 169,348.61 ንብረት ክፍል ሰራተኛ የነበሩት ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- **በደሴ ዙሪያ ወረዳ የጉጉፍቱ አጠ/1ኛ ደረጃ ት/ቤት** ብር 129,070.60 የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የነበሩት በስማቸው ተረክበው ከ30/5/2007-30/7/2008 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ ጉድለት፣
- **የሳይንት አጅባር ወረዳ የውሃና ኢነርጅ ልማት ጽ/ቤት** ብር 91,794.52 የንብረት ክፍል ሰራተኛ የሆኑት ከ12/09/2006-17/06/2007 ዓ.ም ድረስ ወጭ ያደረጓቸው የግንባታ ማቴሪያሎች ሲመዛዘኑ የተገኘ የንብረት ጉድለት ብር 52,606.78፣የንብረት ክፍል ሰራተኛ የሆኑት ከ12/09/2006-17/06/2007 ዓ.ም ድረስ ወጭ ያደረጓቸው የግንባታ ማቴሪያሎች ሲመዛዘኑ የተገኘ የንብረት ጉድለት ብር 15,595.64፣የንብረት ክፍል ሰራተኛ የሆኑት ከ12/09/2006-17/06/2007 ዓ.ም ድረስ ወጭ

ያደረጓቸው የግንባታ ማቴሪያሎች ሲመዛዘኑ የተገኘ የንብረት ጉድለት ብር 21,690.95፣የንብረት ክፍል ሰራተኛ የሆኑት ከ12/09/2006-17/06/2007 ዓ.ም ድረስ ወጭ ያደረጓቸው የግንባታ ማቴሪያሎች ሲመዛዘኑ የተገኘ የንብረት ሂሳብ ጉድለት ብር 1901.15፣

- **አዴት ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ** ብር 61,211.99 የኮንስትራክሽን ሾፕ ቴክኒሽያን የነበሩት ከ18/6/2001-30/4/2005 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ ጉድለት፣
- **የቦረና ወረዳ ገን/ኢኮ/ትብ/ጽ/ቤት** ብር 22,889.54 ለ018 ቀበሌ ለሽድ ግንባታ አገልግሎት የሚውል አሸዋና ድንጋይ ከተገዛ በኋላ ለግንባታ አገልግሎት ውሎ ከተረፈ ላይ የተገኘ የንብረት ሂሳብ ጉድለት፣
- **አስፋው ወሰን አልጋ ወራሽ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት** ብር 17,752.00 የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ከ01/11/2007-30/2/2010 ዓ.ም በስማቸው ተረክበው ያስተዳደሩት የንብረት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ ጉድለት፣
- **በወረኢሉ ወረዳ የኪሬ ማርያም አጠ/1ኛ ደረጃ ት/ቤት** ብር 11,400.00 ለትምህርት ቤቱ ግንባታ የተረከቡት አሸዋ እና ስራ ላይ የዋለው ሲመዛዘን የተገኘ የንብረት ሂሳብ ጉድለት፣
- የደብረ ብርሃን ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 4,589.44 ንብረት ክፍል ሰራተኛው ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የንብረት ሂሳብ ጉድለት፣

በመሆኑም ከንብረት ሰራተኞች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካከትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 28,154.54 ተመላሽ መደረጉ የተገለፀ ሲሆን ብር 12,596,883.72 (92.29%) በፍታብሔርና በወንጀል ክስ እንዲሁም ማስረጃ በማሰባሰብ ሂደት ያለ መሆኑ ከፍትህ አካላት የተገለፀልን ሲሆን ውሳኔው እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

ክብርት አፈ-ጉባዔ!

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ኦዲት ሪፖርት፤

2.1 እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች፤

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመ/ቤታችን መደበኛ ኦዲት በተደረገ 248 መ/ቤቶች በተደረገው የክትትል ኦዲት ወደ ኋላ ባሉ የተለያዩ በጀት ዓመታት ሂሳባቸው በመ/ቤታችን ኦዲት ተደርጎ በተገኙ ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምት እርምጃ አወሳሰዱ በክትትል ኦዲት ሲጣራ በአንዳንድ መ/ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ቀን ሰኔ 13/2010 ዓ.ም ድረስ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው የኦዲት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2.1.1. የ2006 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤት

- **ጎንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ተወስኖ ያልተሰበሰበ ግብር ፣ታክስና አስተዳደራዊ መቀጫ ብር 2,177,340.69፣በውል ስምምነት መሰረት ያልተሰበሰበ የሊዝ ክፍያ ብር 70,304.40፣
- **ገንዳ ውሃ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ተወስኖ ያልተሰበሰበ ግብር ብር 30,347.57፣

2.1.2. የ2007 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤት

- **ቻግኒ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በግንባታ ውል ስምምነት መሰረት ከቅጣት ያልተሰበሰበ ሂሳብ ብር 21,571.45፣
- **ጃዊ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ህጋዊ ደረሰኝ ያልቀረበለት ወጭ ብር 46,040.00፣
- **ጃናሞራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በተለያዩ ቀበሌዎች ስሚንቶ ለተጓጓዘበት የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተከፈለ ሂሳብ ብር 61,300.00፣
- **ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ ብር 44,935.00፣
- **ነፋስ መውጫ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** የከተማው የውስጥ ለውስጥ የኮብል ስቶን መንገድ ቅድሚያ ክፍያ ወስደው ስራውን ያቋረጡ የስራ ተቋራጭ ከሰሩት በላይ የተከፈለ ሂሳብ ብር 212,814.20፣
- **ደቡብ ወሎ ዞን አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ ብር 19,483.20፣አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 15,586.00፣
- **ጁሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ባልተሟላና ብቃት በሌለው ማስረጃ በወጭ ተይዞ የተገኘ ሂሳብ ብር 627,494.72፣ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የወጪ ሰነዶች ብር 547,107.00፣
- **ደዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ገቢ ያልተደረጉ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ደረሰኞች 45 ጥራዝ፣
- **አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 18,181.91፣ለኦዲት ስራ

ያልቀረቡ የወጪ ሰነዶች ብር 17,262.00፣በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ክፍያ ብር 83,988.34፣ ያለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 14,450.00፣ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የስልጠና አበል ብር 56,450.00፣

- **ባቲ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 12,581.36፣በብልጫ የተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 859,194.10፣ደረሰኝ ሳይቀርብለት የተከፈለ ወጪ ብር 12,301.39፣ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የወጪ ሰነዶች ብር 1,202,447.89፣

2.1.3. 2008 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤት

- **አብክመ ንግድ ኢንዱስትሪ ገበያ ልማት ቢሮ** በጎንደር ከተማ ለሚገነባው የኢንዱስትሪ ሸድ ግንባታ ላልተሰራ ስራ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 900,735.75፣
- **አብክመ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን** በባህር ዳር ከተማ ለሚያስገነባው የማረሚያ ቤት ግንባታ ቁጥጥር ስራ ለአማካሪ ድርጅት በብልጫ የተከፈለ ብር 55,414.15፣
- **እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ተወስኖ ያልተሰበሰበ ግብር አስተዳደራዊ መቀጫ ብር 38,941.62፣ለኦዲት ያልቀረበ የእርሻ ስራና መሬት መጠቀሚያ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 95,700.00፣
- **ሸበል በረንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ክፍያ ብር 51,671.25፣
- **ጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ያልተሰበሰበ የአገልግሎት ክፍያ ብር 77,250.00፣
- **ደጀን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ያልተቀነሰ የንግድ ስራ ትርፍ ግብር ብር 10,342.39፣
- **ላይ ጋይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ** ያላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ ብር 10,034.26 ፣
- **ነፋስ መውጫ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** በብልጫ የተፈፀመ የግንባታ ወጭ ሂሳብ ብር 112,009.73፣የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ብር 897,151.95፣
- **ጭልጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ያልተሰበሰበ የሽልማት ገቢ ብር 24,744.96፣የግንባታ ስራ ስፍር ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 378,159.74፣
- **እንጅባራ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ** አንድ ባለሙያ ባልተፈቀደ የስራ መደብ ተመድበው የተከፈለ የማትጊያና ትርፍ ስዓት ክፍያ ብር 10,511.00፣
- **አብክመ ሴቶችና ህፃናት ቢሮ** ያልተሰበሰበ የአገልግሎት ክፍያ ብር 10,500.00፣
- **ሳይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል** ከሽልማት ያልተቆረጠ የስራ ግብር ብር 16,719.24፣ በብልጫ የፀደቀ ወጭ ብር 14,407.97፣
- **ተሁለደሬ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል** ለኦዲት ያልቀረቡ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ብር 22,397.00፣ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 69,334.20፣ለሚመለከተው ፈሰስ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት

የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 112,496.47፣አላግባብ የተፈፀመ ወጭ ብር 45,854.00፣ በተጭበረበረ ደረሰኝ የተከፈለ ወጭ ብር 308,588.40፣ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈጸመ ወጭ ብር 94,896.67፣የተፈጥሮ ሚዛኑን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ የተገኘ የተከፋይ ሂሳብ ብር 865,100.53፣

- ***ቦረና ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል*** ከሽልማት ክፍያ ላይ ሳይቀነስ የቀረ የስራ ግብር ብር 19,119.10 ፣አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል ብር 23,500.00፣
- ***ወግዲ ወረዳ ነ/ፋይ/ድ/ስ/ማዕከል*** አላግባብ የተከፈለ የድጎማ ወጭ ብር 20,000.00፣ ከሽልማት ክፍያ ላይ ተቀንሶ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 26,071.00፣
- ***ሀይቅ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ከሽልማት ክፍያ ላይ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 23,023.02፣
- ***መካነሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ባልተሟላና ብቃት በሌለው ማስረጃ የተፈጸመ የካሳ ክፍያ ብር 688,532.36፣
- ***ዋግ ኽምራ ብሄረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ከሽልማት ክፍያ ላይ ሳይቀነስ የቀረ የስራ ግብር ብር 78,901.56፣
- ***ጋዝጊብላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ባልተሟላና ብቃት በሌለው ማስረጃ የተከፈለ ሂሳብ ብር 33,600.00፣ ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የመደበኛ ሂሳብ ብዛት 9.2 ጥራዝ እና የስፖርት ምክር ቤት 26.56 ጥራዝ የገቢ ደረሰኞች ብር 33,690.26፣ ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የሴፍትኔት የወጭ ሂሳብ ሰነዶች ብር 26,244.00፣
- ***ሰሜን ወሎ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ከሽልማት ክፍያ ላይ ያልተቀነሰ የስራ ግብር ብር 11,875.08፣
- ***ጉባ ላፍቶ ወረዳ /ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ከሽልማት ክፍያ ላይ ያልተቀነሰ የስራ ግብር ብር 40,236.96፣
- ***ዋድላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ 10 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት ደረሰኝ ብር 102,260.00፣
- ***የራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ጽ/ቤት በውለታው መሰረት ካልቀረበ የህንጻ መሳሪያ ግዥ ላይ ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 12,591.03፣
- ***ጅሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 17,932.74፣የተጨማሪ እሴት ታክስ ሪፖርት ያልቀረበለት ወጪ ብር 91,906.05፣ደረሰኝ ሳይቀርብለት የተከፈለ ወጪ ብር 397,405.75፣
- ***ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 36,851.64፣ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 1,214,211.89፣
- ***አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል*** የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብለት የተፈጸመ ክፍያ ብር 1,384,548.85፣ ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የስፖርት ምክር ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 73,490.67፣ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የሴፍትኔት የወጪ ሰነዶች ብር 97,081,534.73፣ባልተሟላ ማስረጃ የተከፈለ ሂሳብ ብር 10,875.00፣ከሽልማት ክፍያ ላይ ያልተቀነሰ የስራ ግብር ብር

6,502.60፣ ከክፍያ ላይ ያልተቀነሰ የስራ ገቢ ግብር ብር 16,424.40፣

- **ባቲ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ባልተሟላ ማስረጃ የተከፈለ ክፍያ ብር 557,981.64፣የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ክፍያ ብር 110,455.64፣ያለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 12,496.00፣
- **ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈጸመ ግዥ ብር 37,659.00፣አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበልና የስልጠና አበል ብር 16,620.00፣በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ መቀጫ ብር 12,808.80፣ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የስፖርት ምክር ቤት ገቢ ብር 32,850.00፣
- **ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** አላግባብ ለአመራሮች ስልጠና የተከፈለ ሂሳብ ብር 33,199.50፣ያለአግባብ የተከፈለ የአካፋ ኪራይ ብር 107,927.90፣የስራ ዝርዝር ሳይቀርብለት የተፈጸመ ክፍያ ብር 354,644.01፣
- **ሚዳ ወረሞ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ለፖሊሶች ድጎማ ከተከፈለ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 23,112.90፣
- **መራ ቤቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** የልኬታ ወረቀት ያልቀረበለት የግንባታ ክፍያ ብር 66,400.14፣ ባልተሟላ ማስረጃ በወጪ ተይዞ የተገኘ ብር 41,217.25፣
- **መንዝ ቀያ ገብሬል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 16,513.30፣
- **መሀል ሜዳ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ከሽልማት ክፍያ ላይ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 24,143.64፣ በብልጫ ተከፍሎ መሰብሰብ የነበረበት ብር 14,433.41፣
- **አጣዬ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 18,015.40፣
- **ደብረ ብርሃን ማረሚያ ቤት** ከማበረታቻ ሽልማት ክፍያ ላይ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 84,553.40፣
- **አንፆኪያ ገምዛ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል** ከሽልማት ላይ ያልተቀነሰ የስራ ግብር 52,470.40፣

እነዚህ ከብር 10,000.00 በላይ የሆኑ በ55 መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች በወቅቱ በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሜ እያሳሰብን የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲጠናከር መ/ቤታችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር የሚሰራውን ተግባር አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ክብርት አፈ-ጉባዔ!

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

የኦዲት አስተያየትን በሚመለከት፤

44. የ2009 በጀት ዓመት ሒሳባቸው በመደበኛነት ኦዲት ከተደረጉ 248 መ/ቤቶች ውስጥ ለ14 (4%) ***"ንፁህ"*** የሚል የኦዲት አስተያየት እንዲሁም 215 (67%)" **ከዚህ በስተቀር"**፣ የሚል ኦዲት አስተያየት ያገኙና ‹‹**አስተያየት መስጠት አልተቻለም**›› እና‹‹**አጥጋሚ አይደለም**›› የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች ብዛት ውስን መሆኑ አብዛኞቹ የክልላችን መ/ቤቶች የክልሉን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት አድረገው በጀትን ለመምራት ጥረት እያደረጉ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት

45. የ2009 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት የተደረጉ ተቋማት በምላሽ አሰጣጥ ረገድ እየቀነሰ መምጣጡት ያመላክታል፡፡

የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት

46. የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 5,958,861.73 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 5,923,779.50 ከቀትሞ ገንዘብ ያገኙች በጉድለት የተገኘ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ8 መ/ቤት ብር 649,973.62 የቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ መገኘቱና 63 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

የገቢ ሂሣብን በተመለከተ

47. የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መንከል በ2 መ/ቤቶች ብር 46,020.00 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ሽሸ፤በ5 መ/ቤቶች **ብር 256,337.16** የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይሆን የተገኘ ሲሆን በ79 መ/ቤቶች ብር 99,382,640.47 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ በ11 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 285,183.22 ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ

የሚገባው የንግድ ስራ ትርፍ ግብር ሳይሰበሰብ ተገኝቷል እንዲሁም በ65(20.38%) መ/ቤቶች ብር 42,515,120.57 የያዙ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት

48. የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ108 መ/ቤቶች ብር 1,651,173,172.00 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ላይ በ4 መ/ቤቶች ብር 39,833,489.74 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣መቸ እንደተሰጠ፣ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩ ሳይታወቅ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱና በ46 መ/ቤቶች ብር 497,265,160.61 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

የወጪ ሂሳብን በሚመለከት

49. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ16 መ/ቤቶች ብር 2,521,677.58 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ መገኘቱ፤ በ16 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 5,506,089.40 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት መገኘቱ፤ ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ108(33.85%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት የተፈጸሙ ክፍያዎች በድምሩ ብር 44,222,087.64 አላግባብ ተፈጽሞ መገኘቱ፤ የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው ይህ ባለመደረጉ በ52(16.30%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 50,268,896.58 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤

በ64 (20.06%) መ/ቤቶች የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 25,179,267.38 የወጪ ደረሰኝ /ፋክቱር ሳይቀርብለት □ፍያ ተፈጽሞና ተመዝግበዐ መገኘቱ፤ክፍያዎች የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ26(8.15%)መ/ቤቶች ብር 45,622,027.66 የያዘ የክፍያ ማስረጃ ለኦዲት ሳይቀርብ መቅረቱ፤የዕቃዎች አገልግሎቶች የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ በ140 (43.88%)መ/ቤቶች ብር 119,427,957.14 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓትን የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

የተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት

50. የ2009 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ38 መ/ቤቶች ብር 112,483,522.92 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቸ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ

51. የ2009 በጀት ዓመት ሒሣባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 248 መ/ቤቶች መካከል በ110(44.35%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ሲቀር ኦዲት ከተደረጉ መቤቶች ብር 13,649,559.32 በጉድለትና በማጭበርበር ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡

ክብርት አፈ-ጉባዔ!

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

ከዚህ ቀጥሎ የማሻሻያ አስተያየቶችን አቀርባለሁ፡፡

በዚህ በጀት ዓመት ባቀረብነው የመ/ቤታችን ዕቅድ አፈፃጸም ላይ የተስተዋሉ ውስንነቶች፣ በኦዲት ተደራጊዎች የታዩ ግኝቶች ተሻሽለው የኦዲት ሽፋናችን እንዲያድግና የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር አመራር ሥርዓት መጠናከር እንዲችል የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያቶችን አቀርባለሁ፡፡

የኦዲት ሽፋንን ለማሳደግ ጥራቱን እና ወቅታዊነቱን የጠበቀ ለማድረግ ከአደረጃጀት አንጻር ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

52. በክልላችን ያለው ልማት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጐለበት በመምጣቱ የኦዲት ተደራጊ ተቋማት ብዛትና በጀት እየጨመረ የሚገኝ በመሆኑ የኦዲት ሽፋንኑን ማሳደግን አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ጥራቱንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ ሪፖርት ማቅረብ ወሳኝ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይም ማህበረሰቡ ስለ ኦዲት ሙያ ግንዛቤ በመያዙና የጥቆማ ተሳትፎው በመጨመሩ እንዲሁም ለፍትሃዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሲባል በየደረጃው ካሉ ፍርድ ቤቶችና የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን የሚቀርቡ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች በስፋት እየቀረቡና በተለየ ትኩረት ተይዘው ካልተሰሩ አሁን ባለው አደረጃጀት ከመደበኛው ኦዲት ስራ ጋር ደርቦ በመስራት ለጥያቄው ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት ያላስቻለና ከስራው ጥራትና ብዛት አንጻር ራሱን በተለየ አደረጃጀት መምራት አስፈላጊ አድርጎታል፡፡

ይኸውም የልዩ ኦዲት ስራ ከባህሪው፣ ካስቸኳይነቱና በህግ ፊት ለቀጠሮ የሚፈለግ በመሆኑ፣ ከዓመት ዓመት በስፋት እየጨመረ በመምጣቱና ጊዜ የማይሰጠው ስራ በመሆኑ የመደበኛ ስራውን ሊጋፋ በሚችል ደረጃ ጫና እያስከተለ በመምጣቱ ራሱን በቻለ ዳይሬክቶሬት መምራት ይቻል ዘንድ አደረጃጀቱ ምላሽ እንዲያገኝ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድና ማሻሻያ አስተያየቶች ትግበራ ሊጠናከር ይገባዋል፡፡

53. ኦዲት ተደራጊዎች በምላሽ አሰጣጣቸው እየወሰዱት ያለው እርምጃ አዝጋሚና ተጨባጭ ለውጥ የሚያመጣ ሆኖ ባለመገኘቱ መልስ በማይሰጡና እርምጃ በማይወስዱ፣ በኦዲት አገልግሎቱ እየተጠቀሙ ከዓመት ዓመት በማይሻሻሉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ላይ በየደረጃው በሚገኙ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና የፍትህ አካላት አማካኝነት ክትትል ሊደረግበት እንዲሁም የኦዲት እርምጃ አወሳሰድ ክትትልና ድጋፍ ግብረ ኃይል በየደረጃው በማቋቋምና በማጠናከር የግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡

ይህን ክትትልና ተጠያቂነት ለማጠናከር በመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ (Public Accounts Committee) በክልሉ ምክር ቤት መቋቋም ይችል ዘንድ ከፌደራልና ከሌሎች አቻ ክልሎች የተወሰደው ልምድ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ነው፡፡

54. በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቶቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያገናዘቡ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣ የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር በሌላ በኩል ደግሞ የመ/ቤቱ ስራ አመራር፣የኦዲት ባለሙያዎችና መላው ሠራተኞች በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳያችሁት ታታሪነትና የሙያ ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

ገረመው ወርቁ ካሴ (ረዳት ፕሮፌሰር)

ዋና ኦዲተር

ሰኔ/2010 ዓ.ም

<u>**ባህር ዳር!!**</u>